# አረ ጎበዝ…! ኢትዮጵያ ከጃችን ማምለጧ ይሆን?!!

አትክልት አሰፋ (ከቫንኩቨር-ካናዳ)

እነኝህ የዛሬዎቹ ጉዶች ሀገሬን ሲቆጣጠሩ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነበርኩ። በተለይ የቡትሮስ ጋሊ የአዲስ አበባ ጉብኝት ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አምጸው ስለነበር በየከተማው ብዙ ወጣቶች የተገደሉበት ጊዜ መሆኑን የሚዘነጋ ልብ የለኝም። በጊዜው ደሴ ከተማ የሚገኘው ወ/ሮ ስህን ት/ቤት የተማሪዎች ምክር ቤት አባል ሆኜ ሁለት ሳምንት ት/ቤት ዘግተን መከራችንን አይተን ነበር። በወቅቱ ተጋዳላዮቹ ጋር መሳፈጥ ወይንም ሰብሰብ ብሎ መቆም በጥይት አረር ያስቆላ ነበር። ምን ያስቆላ ብቻ ስምም ያሰጣል። የደርግ ርዝራዥ፣ የወታደር ቤተሰብ፣ ጥቅም የቀረባቸው። አረ ስንቱ…

በዚያን ጊዜ በነበረው የጥምቀት በአል ላይ በሰው ልክ መጠን ነበር የተጋዳላይ ጦር የተሰገሰገው። ሰው ሰብሰብ ብሎ መጨፈር ፈርቶ ራቅ ራቅ ብሎ ቆሟል። አንዱ ደፈር ያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ ለጥምቀት መጨፈር አንከለከልም፤ ዲሞክራሲያዊ መብታችን ነው። በማለት ያስተባብልና ጭፈራው ይጀመራል። በደፋሩ ንግግር የተስማሙትና የሰው መሰብሰብ ያሰጋቸው የወያኔ ወታደሮች ነገሩን በጥንቃቄ ለመያዝ መሳሪያወቻቸውን አቀባብለው ሰውን ሲከተሉ ያየ አወራራጅ(የጭፈራ መሪ) አረ ጎበዝ… ሲል፤ እሕም ነው ይላል የተቀረው ሰው። አረ ጎበዝ ይላል አሁንም በድጋሚ ሁኔታው ያሳሰበው የጭፈራው መሪው በፍርሃት። እህም ነው… ይቀበላሉ እንቅስቃሴውን የሚከታተሉት ተከታዮችም ቀና ቀና ብለው አካባቢውን በጥንቃቄ እያዩ… አይምሩንም ሊጨፈጭፉን ነው… ይላል። እህም ነው.. ይቀበላሉ ሌሎቹ። አረ ጎበዝ ይላል ደግሞ …. ይቀበላሉ መሞትህ ነው…. እንደምንም በማለት ጭፈራውን ቀዝቀዝ ቢያደርጉትም በዛ የጥምቀት በአል የሞቱትን ወጣቶች ማዳን አልተቻለም። እስጢፎ የተባለና ሌላ ሴት ልጅ እስካሁን ከህሊናየ አይጠፉም። መሀል ፒያሳ ላይ በጥይት ጨኸት ቀለጠች…። አብሮ አደጌ ሸዋንግዛውም ሆዱን በጥይት ተበሳ።

እልቂት በልቂት፤ ዲሞክራሲ በዲሞክራጢ እየተተካካ ይሄው ዛሬ ደረስን። ጎበዝ ዛሬ የማወጋችሁ እህም ነው የሚያስብል አይደለም። ግራ ግብት ብሎኝ ግራ ላጋባችሁ እንጂ። መቸም ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው እድገት፣ ካሚዮን መንገድ፣ ህንጻ፣ ጭፈራ ቤት፣ የቆነጃጅቶች ውበትና አለባበስ፣ ስልጣኔና ስይጣኔ ሀገር ቤት ደርሰው መጥተው የሚያወሩላችሁ ብዙዎች ናችሁ። አረ ጎበዝ ነው ነገሩ።

ሀገር ቤት እንዴት ነው አልኩት በቅርብ ከኢትዮጵያ የመጣ ወዳጄን ቤቱ ሄጀ። ትንሽ ተከዝ ብሎ እንግዲህ ሁለት ነገር ነው ያየሁት… ህንጻው ፣ መንገዱን ካልክ? አዲስ አበባ ውስጥ የምታውቀውን ቦታ ጠይቀኝ? አለኝ። ገዳም ሰፈር? አልኩት። ሰፈሬ ትዝ ብሎኝ። በቃ ይሄ ተነስቷል፣ ይሄ እንዲህ ሆኗል። እያለ ህንጻ የተሰራበትንና መንገድ የቀናበትን… አራዳ ጎርጊስ ፊት ለፊት እሳት አደጋ የሚያስገነባውን ህንጻ… ብቻ ምኑ ቅጡ ሁሉም የማውቃቸው ቦታዎች እንዳልነበሩ ሆነው ለውጥ ወይንም 'መተካካት' የተደረገባቸውን አጫወተኝ። እውነቱን ነበር። በዚህ ረገድ የተለወጠ ነገር መኖሩን ላለመቀበል ቆርጦ የተነሳ እርሙን ያውጣ።

በሌላ መልኩ ካየሽው ደግሞ… አለ ይሄው ወዳጄ ሲያወጋኝ። ከኢትዮጵያ ውጭ ልጅ፣ ዘመድ፣ ምናምን የሌለው ሰው ካልሆነ በስተቀር እንዴት ኑሮውን ሊቋቋሙት እንደቻሉ ይደንቀኛል። አንድ ሊትር ጋዝ 15ብር ፣ አንድ ሊትር ዘይት 18 ብር የመግዛት አቅሙ ያላቸው የኔና ያንተ ቤተሰቦች ብቻ ናቸው። ሲል ቀጠለ። ፊቱ ላይ ከልቡ እንዳዘነ ያስታውቃል። ስለ አንድ ኤ ዋን ሰለሚባል ወተት ታሪክም አወጋኝ። እንዲህ ሲል… ለህጻን ልጅ ኤ ዋን የተባለ ወተት የዛሬ አመት 120ና 130 ብር ነበር፤ አሁን 200ብር ነው የምትገዛው። እሱም ጠፍቶ በፍለጋ የተንከራተትኩት ብዙ ቦታ ነው። በማለት ምርር ብሎት ፊቱን አጨፋገገ፤ ለምን የማይገኝ ወተት ለህጻን እንዳስለመዱ ገርሞትና ተናዶ ቤተ ዘመዶቹ ጋር ጠብ እንደገጠመ አወጋኝ።

ነገራ ነገሩ ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነው። ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር የጥቂት ቱጃሮች መፈንጫ ሆና የብዙሀኑ መረገጫና ጠኔ መሰንበቻ የሆነችው በደርግም፣ በንጉሱም፣ ወረድ ካልንም በነገስታቱም ወቅት ነው። የአሁኑን ለየት የሚያደርገው ሰው በተማረበትና በተመራመረበት፣ ችጋር በሀገራቶች እንዲጠፉ ደፋ ቀና የሚሉ ወገኖችና መሪዎች በበዙበት ጊዜ መሆኑ ነው። ለዚያውም ተራራ እያረሰ ለዘመናት ህዝብን መቀለብ ልምድ ያለው የኢትዮጵያን ገበሬ ይዞ ለውጥ ለማምጣት ከባድ ሆኖ አይደለም። እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህችን ሀገር የሚያሰቃያት ሰራተኛ አለመኖርም፣ ራብም፣ ችጋርም፣ በግፍ መሞትም አይደለም ቅን ልቦና ያለው መሪ ማጣት እንጂ። ቅንጣት ታህል ቅንነት ያለው መሪማ ቢኖር አይደለም 19 አመት ሺ አመት ቢገዛስ፤ አይደለም ከመሰረታችን ትግራይ፤ ከእንጦሮጦስስ ቢመጣስ ምን ቁርጥ አድርጎን።

ለትንሽ ሰዎች የሚጨነቅ፤ እፍኝ ለማይሞሉ የጊዜው ባለጊዜ ከበርቴዎች እንጀቱ የሚራራ ሳይሆን ለብዙ ደሃ የሀገሪቱ ክፍል የሚንሰፈሰፍ መሪ ጠፍቶ እንጂ፤ ራሱን ከሌሉና ካለፉ አገዛዞች ጋር እያወዳደረ በጎ ሰርቻለሁ፣ መንገድ ዘርግቻለሁ ሳይሆን አሁን ካለው የአለም ሁኔታ ጋር ለመራመድ ድፍረት ያጣ መሪ ተጋርጦብን እንጂ። ከአፉ መልካም ነገር የማይሰማ ይልቁንም በጸያፍ የንቀት ንግግር የሚለፋደድ መሪ ጥሎብን እንጂ።

አካባቢው በተኮለኮሉ ቱጃሮችና ጨካኞች መዝኖ፤ 86 ሚሊዮን ህዝብ አጠገብኩ የሚል መደደዴ ወርዶብን እንጂ።

ያሁኖቹ ቱጃሮችማ በቅጡ ይታወቃሉ። ብዙ ህዝብ መሀል ጣል ጣል ያሉ ስለሆኑ በደንብ ይታያሉ፤ አዲስ አበባም ሆነ ዋና ዋና የክ/ሀገር ከተሞች፤ ገጠርም ብትገቡ የማን ንብረት ምን እንደሆነ፤ የማን መኪና ታርጋ ቁጥር ለማን እንደተሰጠ፣ የማን ቤት በምን አይነት እምነበረድ እንደተሰራ፣ ዝርዝር አድርገው የሚነግሯችሁ አሉ። ህዝቡ ሁሉን ዘርዝሮ አውቃል። ያሁኖቹ ጉዶች ደግሞ ይሉኝታ እንኳን የላቸውም፣ የጄኔራል ማዕረጉን የደረደረ ወታደር መሀል አዲስ አበባ ላይ ቆሞ ቤት ሲያሰራ ታያላችሁ፤ ሚኒስተሩ ትላልቅ ካሚዮን የሚገዛው ከአብራኩ በወጣች ልጁ ስም ነው፤ ሌላም አለ… ቀዳማዊ እመቤቲቱም አስር ቦታ የምታስጀምራቸውና ያስጨረሰቻቸው ቤቶች ጠሀይ ሞቆታል። ወሎ ሰፈር አካባቢ ታስገነባለች በሚባለው ህንጻ የጦር ሰራዊት የጭነት መኪና የሚገለብጠው አሸዋና ሲሚንቶ… ከሰው አይን ሽፋሽፍት የራቀ አይደለም። ልቀጥል ነው…።

አንዲት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የቅርብ ቤተሰብ ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ ስትገባ አንድ ሚሊዮን ዩሮ ተሸክማ ነበር። ጎበዝ ይህ የምነግራችሁ ውሸት ወይንም የተጋነነ ለማድረግ የታሰበ አይደለም። ውስጥ አወቆች ያጫወቱኝን ነው። ይሄንን ሁሉ የዩሮ ረብጣ ይዛ የገባችው የመለስ ዘመድ ግማሹን ስም መጥቀስ በማያስፈልግ አውሮፓ ለስብሰባ በመጣ ባለስልጣን አሸክማ፤ ያለምንም ፍተሻ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያን የግሙሩክ ጠባቂዎች አሻገረችው። ግማሹን ራሷ ይዛ ስትገባ በቪ አይ ፒ ያስገባቻት አዜብ መስፍን ነበረች። የሚገርመው ዩሮው ሀገር ቤት ከገባ ሳምንት አልሞላውም ምንዛሬ ጣሪያ ነካ ተባለ። እንግዲህ ትርፉን አስሉት። ብሩን እንዴት አገኘችው? ከየት መጣ? እግዜር ይወቀው። ግን ብሩ ማለቴ ዩሮው ሀገር ቤት ገብቷል። አሁን… እህም ነው… አስብላል።

አንዲት ከዚህ መንግስት ጋር የተሞዳሞደችና ሀብቷ ተዝቆ የማያልቅ የትግራይ ሴት 7 ሚሊዬን ብር ልትገዛው የተስማማችውን ቤት ሻጩ በምንዛሬ ለውጥ ምክንያት 9 ሚሊዬን ነው የምሸጠው ቢላትና ሀሳቡን ቢቀይር ዘጠኙንም በእጇ ቆጥራ ነው የከፈለችው። ምክንያት… ወደደችዋ! በቃ ወደደችው! ብሩ በእጇ አለ። ገዛችው። ከየት መጣ?፣ እንዴት በጣ? አረ ጎበዝ… ብቻ ነው የሚያሰኘው።

ይህንን አይን ያወጣ ጉድ ጉያችን ተሸክመን ነው የምንኖረው። የምንበላው፣ የምንጠጣው፣ የምንናቆረው፣ የምንዘላለፈው። በቤተ መንግስት ሰዎች ግብዣ ሶስት ቁጥር ማዞሪያ አካባቢ በሚገኘው የጎልፍ ክለብ ያቀና አንድ ሰው - ዳንኪራ ሲያስመታ የነበረ የትግርኛ ተጫዋች በሽልማት ብዛት ልብሱ በረብጣ ሲሞላ፣ ሌሎቹን ዘፋኞች የሚሸልም ጠፍቶ የመለስ እህት ሁኔታውን አይተውና ተሰምቷቸው ነው ይህንን 300 ብር ለዛ ለአማራው ዘፋኝ ስጡት ያሉት። ልቀጥል…?

በነገሬ ይህ ዘር የሚሉት አባዜ እኒህ ጉዶች አምጥተው ወሸቁብን እንጂ ስለ አካባቢ ማውራት የሚወድ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። ለነገሩ አሁንማ ሀገር ወዳዱስ በዚሁ ተጠምዶ የለ። አንድ ሸዌ ወይንም ጎንደሬ፤ ወሎዬ አልያም ወለጌ እንዲያም ካለ የሀረር ሰው ካጠፋ ወይንም የራሱን መንገድ ከተከተለና ሌላ የአካባቢው ሰው ያንን እምነቱን ከተቀበለው ሸዌ ወይንም ጎንደሬ፣ ሀረሬ፣ ወሎዬ ስለሆነ ነው እያልን መፈረጅ ከተማርን ሰነባብተናል። አንድ የነቀምት ነዋሪ ወዳጅ ቢኖረኝና ያ ወዳጄ የሚያራምደውን ከተስማማሁበት ጓደኛው ስለሆነ ነው የደገፌው። ሆኗል ፍረጃው። አረ ጎበዝ … እህም ነው። ሆኗል የኛ ነገር።

እናም እንደወያኔ ሰዎች በዘር ከተተበተብን ሰንብተናል። እየባሰንስ ሳይሆን ይቀራል?? ፋታ ወስደን ካሰብነውማ ከማውቀው ጓደኛየና ከሚቀርበኝ የሰፈሬ ልጅ ሌላ ማነው ሀሳቤን የሚረዳልኝ። ቁጥር ከአንድ ነው የሚጀምረው። ነው ወይንስ አንተ የሰፈሬ ልጅ ስለሆንክ አላናግርህም፤ ዘረኛ እሆናለሁ። አንተ ጓደኛየ ስለሆንክ ሀሳብህን አታምጣብኝ ልንባባል ነው። አረ እየተስተዋለ።

ይሄንን የዘር ትብትብ ለመበጣጠስ የተለያዩ ድረ ገጾችንና ራዲዮ ጣቢያዎችን በመክፈት ደፋ ቀና የሚሉ ወገኖቼ ቸሩን ለናንተ ያርግላችሁ ከማለት ሌላ ምን ማለት ይቻላል። በፓልቶክ ክፍል ከፍታችሁ የምታወያዩ ወገኖችስ ምን ላድርጋችሁ? ቸሩ ቸር ለናንተ ያድርግ ከማለት ውጭ። እናንተ የተማራችሁ ወገኖቼ ግን ምርር አድርጋችሁኛልና ልራገም ነው?። ፈሪዎች ሆናችኋል። እኔ ፈሪ የማውቀው መንጌን ነበር። መለስን ነበር… ሳይጠየፉ በሰው ልጅ ደም ላይ የሚራመዱ ፈሪዎች። በህዝባቸው ፊት ደፍረው የማይንጎራደዱ እኩይ ፈሪዎች። ከአፋቸው መልካም ነገር የማይወጣቸው የአስተዳደግ ደሃ። ፈሪዎች። እነመለስ ናቸው። የሀገሬ ምሁራኖችም አብዛኞቻችሁ እንደነሱ ሆናችኋል። በፍራቻ ተጠምዳችሁ ኑሯችሁን የምታግበሰብሱ ፈሪዎች።

እንደኔ እንደኔ ፓልቶኮችና ድረ-ገጾች የተቻላቸውን የሚያደርጉ ልጓም የሌላቸው የጋሪ ፈረስ የሆኑት ምሁራኖች በዙሪያው ለመሳተፍ ድፍረት ስላጡ ይመስለኛል። ፓልቶክ ብዙ ሊተቹና ሊያድጉ የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉት ሁሉ ብዙ ሊነጥሩ፣ ሊበራዩ የሚገባቸው ሀሳቦች የሚፈልቁበት የሀሳብ ኢንዱስትሪ ነው። የፓልቶክ ቤተሰቦች ሳይተዋወቁ የተጎዳኙ ደፋሮችና ልበሙሉዎች ያሉበት… ልቀጥል ነው?…ቀጥል ካላችሁኝ ብዙ ብዙ

እላለሁ። ነገር ግን ሊጠኑና በአንክሮ ልናያቸው የሚገቡ ጉዳዮች በፓልቶክ ውስጥ አሉ። ግን ግን ምሁራን አላገኙም። ግዴታ ምሁራን ብቻ አይደለም.. አስተዋይ ሰው ያላያቸውም ጭምር እንጂ። እነዚህ ሰዎች ድፍን ስድስት አመት ይሄው በገንዘብም፣ በሞራልም ኢትዮጵያን ከልባቸው ለመታደግ የማያደርጉት ጥረት የለም። አንድ ነገር ግን ጎሏል። እሱም የሚፈልቁት ሀሳቦች ፍሬ እንዲያፈሩ፣ እርስ በርስ ተጋግለውና በራሳቸው ንግግር ረክተው እንዳይቀጩ ሊያደርጋቸው የሚችል ሀይል አጥተዋል። ሁሉም ያወራል፣ ይናገራል፤ ራሱ በተናገረው ሌሎችንና ራሱን ያረካልና ጥ ግ ብ ይላል አለቀ። ሌላ ቀን... ሌላ ወሬ...

ላብራራው ድረ ገጾችና ፓልቶኮች ላይ የምናነባቸውና የምንሰማቸው እንክርዳዱን አውጥተን ማለቴ ነው። መታሸት፣ መበራየትና መንጓለል ይገባቸዋል። ከዛም ለቀጣይ እንቅስቃሴ እንዴት ይረዳሉ? በምን አይነት ሁኔታ ይታረም?፣ ጉዟችን ወዴት ይሁን ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይመጣል። ሰዎችዬ በደንብ ማሰብና ሁለት ጊዜ መረዳት ከቻልን ወያኔ ኢህአዴግ በሀገራችን ተንሰራፍቷል፤ በሀገሪቱ ትክክለኛ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን በሚፈልጉ ወገኖችና በወያኔ ኢህአዴግ መካካል ትልቅ... እጅግ ት...ል.....ቅ ክፍተት ይታያል።

ድፍር ብዬ እነግራችኋለሁ ስድስት ወር፣ አንድ አመት፣ ሁለት አመት ቀራቸው እያልን ጊዜ የምንጠብቅበት ሁኔታ ማብቃት አለበት። ይሄው ለስድስት ወር የቀጠሩን መሪዎቻችን ጋር አምስት አመት ልንቆጥር ነው። ይሄው የ97 ምርጫ አልፎ የ2002ቱ ተተካ። በእርግጠኝነት እናገራለሁ! በ2007ትም ምርጫ ከተደረገ እንዲሁ በራሳችን ወሬና ንግግር እየረካን፣ እከሌና እከሌ በየመድረኩ እየተዘነጣጠሉ፣ ሁለት አልበቃ ብሎ ለሶስት እየተፈረከስን እንደርስበታለን። ያላየነውን የተስፋ ዳቦ እንደቋመጥን... መሄዴ ነው? ልቀጥል...? እሱ አይደንቀኝም የ2012ትም ወያኔ ዘልቆ "ምርጫ" አለ ብለን እንዲሁ እንዳንጨምረው ስጋቴ ብዙ ነው። ተስፋ ቆርጬ ተስፋ ላስቆርጥ አይደለም እንደ አያያዛችንና እንደ አያያዛቸው ከቀጠልን ከዚያ አናመልጥም። በመሀል ያለውን ትልቅ ክፍተት ለመሙላት ዝግጅቱ አሁን መጀመር አለበት ለማለት ነው። አሁን።

ይሄው 19 ዓመት ሙሉ ዛሬ ነገ ስንል የትግል ስልታችን እንኳን ሳይጠራ ወይ በየሀሳቦቻችን እንዳንጓዝ ሳንከባበር ሃያኛውን ግም-ቦት የፊታችን እንይዘዋለን። አረ ማስተዋል ይስጠን!። እህም ነው አያስብልም ብላችሁ ነው።

ያለፉትን ጊዜያት ያስመረረኝ ጭቅጭቅ ሰላማዊ ትግል፣ የጫካ ትግል፣ እስካሁን ሊገባኝ ባይችልም ሁለ ገብ ትግል ስንል ነው የኖርነው። ሁሉንም ሳንይዘው፤ ሁሉም እያለፉ ነው። ምን እያለፉ እያለፉብን ነው እንጅ። አንዱ ጓዴ እንደሚለውና እኔም ራሴ እንደማምንበት እስኪ ሁላችንም በየፊናችን እንጓዝ። በቂ ሀይል ማፍራት ይቻላል እኮ ጎበዝ። ሰማኒያ ምናምን ሚሊየን ህዝብ የተሸከመች ሀገር ናት ያለችን። ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች በስደት ያሉባት እናት ናት የወለደችን። ለሁላችንም በቂ ኃይል አለ። የምን መስገብገብ ነው። እስቲ ሁሉንም ለኔ የምንለው የልጆች ጨዋታ ያብቃ። አፍ'ኝ ብበላ ለድንቡሎ ነው። ስለውነት ብለን የየራሳችንን ከሰራን ሁሉንም መጠቀም እንችላለን ባይ ነኝ።

የምን ሰበብ ማብዛት ነው አንዱ የኢህአፓ አባል የሆነ ጥሩ ወዳጄ 'ያኔ ቅንጅት ያገኘውን አንድ ሚሊዮን ዶላር እኛ ብናገኘው፤ የትጥቅ ትግሉን እንጀምርበት ነበር' አለኝ። በታላቅ ቁጭት። እኒህ ሰዎች ያማቸዋል እንዴ? አልኩ ለራሴ። አንድ ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት የሁለት አባሎቻቸውን ቤት መሸጥ ነው፣ ለታጋይ ቤት ምን ይሰራለታል። ዋሽንግተን ዲሲ አለ የሚባለው ህንጻቸውም አለ፣ ብቻ ያላሰብኩት ነገር የለም። በኋላ ሲገባኝ ቅንነት ጎሎ ካልሆነ በቀር ኢህአፓ አንድ ሚሊዮን ብር ጎሎት ጫካ መግባት ተሳነው ማለት ያስጸይፋል። ኢህአፓም፣ ግንቦት ሰባትም፤ የሰላማዊውም፤ የጫካውም ሳይነቋቆሩ ከሰሩ ነገሮች በቀለሉና በስራቸው ፍርድ በሰጠናቸው።

ሰላማዊ እንቅስቃሴ በ1997 ለውጥ አምጥቶ በአይኔ በብረቱ ስላየሁና ከዛ በፊት በአገር ቤት የነበሩትን አፈናዎች ምስክር ስለሆንኩ ለሀገሬ ለውጥ ማምጫ መንገዱ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ነው ብዬ በጽኑ አምናለሁ። አሁን ያለው አፈና ከ96 በፊት ካለው በከፊል ቢለይም አሁንም ተግተን ከሰራን 97ን መድገም ይቻላል። ባይ ነኝና እኔንና የኔን ሀሳብ የሚከተሉትን ተውን። የኛን ጎዳና እኛው እንጓዝበት። በዛው ልክ ደግሞ በትጥቅ ማስደንገጥ አለብን ስንሞት ዝም ብሎ ማየት አግባብ አይደለም። እየተፋለምን ብናልቅ ይሻላል ብለውና በጥይት መጥቷል በጥይት ልዋጋው የሚሉ ሀይሎችም ስንቃቸውን ያዘጋጁ። የግል ወዳጆቼ የሆኑ ትጥቅ ትግል ያዋጣል ብለው የሚያምኑና ነገ ዱር ግቡ ቢባሉ ያለምንም ማወላወል ትምህርቴን፣ ቤቴን ሙሽቴን፣ እናቴን ሳይሉ ለመጓዝ የተዘጋጁ ውድ ጓደኞች አሉኝ። ግን ሀሳቤን ያከብራሉ፤ እኔም ሀሳባቸውን ባልደግፈውም አከብራለሁ። በምትለው ባልስማማም የምትለውን እንድትል እታገልልሀለሁ ነው የሚሉት ፈረንሳዮቹ?።

እውነት እንነጋገር ከተባለና የሞራል ነገር ከተነሳ ሀገር ቤት የራሱን ህገ መንግስት የማያከብር ሀይል ጋር የሚፋለም የሰላማዊ ትግል አርበኛ በምን መመዘኛ ነው ትጥቅ ትግልን የሚባርከው። በምንስ ሞራል ነው ስለ ትጥቅ ትግል በጎነት የሚሰብከው። ወያኔ ደደቢት ሲወርድ መኢሶንን ቡራኬ ጠይቆ ነበር እንዴ? ወያኔ

ኢጫትን እባክህ ጫካ ልሂድ ነው ጎበዝ በለኝ። ብሎት ነበር እንዴ? በቃ መግባት መግባት ነው። የምን የናቴ መቀነት... ነው።

በሰላም መንገድ እጓዛለሁ የሚሉ ወገኖች ለመጭው 2008 ዓ.ም. 'ምርጫ' ካለ ራሳቸውን ያዘጋጁ። ብር ይሰብስቡ አጀንዳቸውን ያጽዱ፣ ከህዝብ ይወያዩ፣ ጥርጊያቸውን ማንጠፍ ዛሬ ይጀምሩ። ለዚህም ውጭ ያለነው ድርሻ ጠገራ መስጠት ነው። አለቀ። የተቀረው የአለም ማህበረሰብ ስለኢትዮጵያ እንዲያውቁ ሎቢ ማድረግ ነው። እናድርግ። በትጥቅ ትግል የሚያምኑትም አስፈላጊ የሚሉትን አዘጋጅተውና ቤዛቸውን መስርተው ጉዟቸውን ያቅኑ። ሁለገቡም እንዲሁ ግቡን የሚያሳካበትን መንገድ ይፍጠር።

ይህንን ለማድረግ ግን ከፓልቶኩም፣ ከድረ ገጾችም ከሰው አፍም፣ በስብሰባዎችም፣ በየራዲዮ ጣቢያዎችም የሚወለዱ ሀሳቦችን የሚያበራይ አንድ ግብረ ሀይል ያሻል። ወይ ምሁራኖች አለያም ማስተዋል የሚችሉ ሰዎች ሰብሰብ ብለው ጥርጊያውን ያብጁ። ረጋ ብለን ማሰብ ካልቻልንና ከድል በፊት ድልን ከጨበጥን እንዲሁ እንዳወራን ወዳጄ አባኪያ እንደሚለው ኢትዮጵያ ከጃችን እያመለጠች ነው። እስቡት ትንሽ የተስፈኝነት ልብ ይዘን የጫካ፣ የሰላም፣ ምናምን... እያልን ስንጣላና ስንታረቅ ያጠፋነውን ጊዜ። እኔ ግንቦት ሰባትን ከሚደግፈው ደጉ ወዳጄ ልጅ ተክሌ ምን ያጣላኛል። ግባችን አንድ፤ መንገዳችን ልዩ። እኔም ኢትዮጵያዊ እሱም ኢትዮጵያዊ። ያለምርጫ፣ ያለ ምክክር የተሰጠን ማንነት። የማይነቀል የማይበጠር ማንነት። አረ ጎበዝ ነው ያለው ያ ሰው...? ልቀጥል...?። ለጊዜው በቃኝ።

እስከዛው ቸር ለሁላችን